የሰ/መ/ቁ.70801

የካቲት 30 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማዉ ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ዋት ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህበር - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፎዚያ ቃዲ - የቀረበ የለም

መዝገቡ የተቀጠረው፤- ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የፍ/ቤት ውሳኔ በተከራካሪ ወገኖች ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ክልል ወሰን ሊያልፍ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ለይቶ ተገቢውን ዳኝነት በመስጠት በሚል የቀረበ ነው፡፡ የጉዳዩም መነሻ የአሁን አመልካች በሥር የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በግዥ ባገኘሁት የንግድ ድርጅት ላይ የአሁን ተጠሪ ሁከት የፈጠሩብኝ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ መሥርቷል፡፡

ተጠሪም ባመለከተው ክርክር የተነሳበት ንብረት ሊገመት ስለሚቻል ተገምቶ ተገቢው የዳኝነት ገንዘብ ተከፍሎበት ሊቀርብ ሲገባ ይህንኑ ሥርዓት አሟልቶ የቀረበ አይደለም፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረበው ውል የብድር እንጂ የሽያጭ አይደለም፡፡ መፃፍ ስለማልችል በተንኮል የተዘጋጀ ካልሆነ በቀር በእኔ የተደረገ አይደለም ስለሆነም ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ በህግ ፊት በማይፀና ውል ንብረቱ በእጅ ገብቷል ማለት ስለማይቻል እና በህግ ማሟላት የሚገባውን ሂደት ባላሟላ ውል ደግሞ በሁከት ክስ ማስፈጸም አይቻልም፡፡ ስለሆነም ክሱ በፍ/ብ/ሥ./ሥ/ሕ/ቁ 33(2) መሰረት ውድቅ ነው የሚል ዳኝነት ሰጥቶበታል፡፡

በዚህም የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ይግባኝ ተጠይቆበት በበላይ ፍ/ቤቶች የሰበር ሰሚ ችሎቱን ጨምሮ በየደረጃው ተቀባይነትን አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ዳኝነት ላይ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚልበትን ዝርዝር ነጥቦች አመልካች በመጥቀስ የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ የተነሳ ሲሆን፤ ተጠሪም ከላይ በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው ነጥብ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክራቸውን አጠናቀዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በከሳሽነት የተሰየመ ወገን አንድ ንብረት በአንድ ህጋዊ ተግባር ሳቢያ ወደ እጄ ገብቷል በይዞታ ላይ እያለ ሁከት ተፈጠረብኝ የሚል ክስ ትክክለኛውን የሁከት የህግ ፅንሰ ሀሳብ ተከትሎ ማቅረቡ ከተረጋገጠ፤ ለዚሁ ክስ በተከሳሽነት የተሰየመው ወገን ከተሰማ በኋላ በፍ/ቤቱ ሊሰጥ የሚገባው ዳኝነት ሁከት ተፈጥሯል ይወገድ፤ ወይም የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት የሚወሰን እንጂ በከሳሹ እጅ ሊገባ የቻለበትን ህጋዊ ተግባር ለመመርመር የሚያበቃ ወይም የሚያስችል ምክንያት አይኖርም፡፡ ከሳሹ የክሱን ምክንያት ዘርዝሮ ሊያገኝ የሚገባውን ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 224 ሲጠይቅ፤ ውሳኔው ይህንኑ የጠየቀውን ዳኝነት ማግኘት የሚቻል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለይቶ ማዘዝ ስለሚገባ የወረዳው ፍ/ቤት ሁከት የተፈጠረ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም ካለ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት መወሰን ሲገባው ከዚህ አልፎ በሌላ የክርክር መስመር ታይቶና ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ሁሉ አካቶ ያለ ቦታው የሽያጭ ውሉ ዋጋ ያለው ነው? ወይስ አይደለም? በሚለው ላይ ዳኝነት መስጠቱ ከተጠየቀው ዳኝነት ክልል የወጣ በመሆኑ ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የአሁን አመልካችም በክስ ማመልከቻው ዘርዝሮ ያቀረበው እና የጠየቀው ዳኝነት ተዳምሮ ሲታይ በሽያጭ ውል ምክንያት በእጁ የገባው የንግድ ድርጅት በተጠሪ ተወስዶበት ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 226 (3) እንደተመለከተው የተወሰደን እና ተለይቶ የታወቀን ንብረት ለማስመለስ የተፈለገ እንደሆነ የዚህኑ ንብረት ዋጋ ተገምቶ የሥረ-ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ተገቢውን በመክፈል ክሱን አቅርቦ በዚሁ የክስ መስመር ተገቢውን ክርክርና ንጥጥር ተደርጎ ተገቢውን ዳኝነት ማግኘት ሲገባ በሥር የወረዳው ፍ/ቤት ክስ የቀረበበት መንገድ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149 እንደተመለከተው በሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ሊስተናገድ የሚገባው ጉዳይ በንብረት ላይ የተፈጠረን ሁከት ለማስቆም (cessation of intereference) ወይም ከሁከት መፍጠር ተግባሩ እንዲታገድ (injuction) ለመጠየቅ እንጂ የተወሰደን ንብረት እንደገና ወደ እጁ ለማስገባት የሚያስችል አይደለም፡፡

ከእነዚህ ሁለት ሐተታዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች በየደረጃው በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በዚህ ጉዳይ የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 45352 በ26/4/03፤ ይግባኝ ሰሚው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10876 በ16/5/2003 ዓ.ም. እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 129205 በ11/08/2003 ዓ.ም የሰጡት ዳኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአሁን ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን ንብረት በሽያጭ ውል ካገኘ በኋላ በተከሳሽ ድርጊት ከእጁ ወጥቶ ከተገኘ ወይም በተከሳሽ ቁጥጥር ሥር ይገኛል ካለ የህንኑ የሽያጭ ውል ያለውን መነሻ አድርጎ ንብረቱን መልሶ ወደ እጁ ለማስገባት እንደ ሥርዓቱ ዳኝነት የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው ብለናል፡፡ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ የሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ሳቢያ ለወጣው ማናቸውም ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ